# 5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጎዳና ላይ ሩጫ

## የውድድር ሕግና ደንብ

**የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን**

ታህሳስ 7/2011 ዓ.ም

ኦሮሚያ ቢሾፍቱ

# 5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር

## አጠቃላይ መረጃ

- የውድድሩ ቀን፡- ታህሳስ 7/2011 ዓ.ም.
- የውድድሩ ቦታ፡- ኦሮሚያ ኪሸፍቱ
- የውድድሩ ተሳታፊዎች፡- ክልል፣ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች፣ ማዕከላትና ተቋም
- አዘጋጅ፡- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን


<u>አድራሻ</u>

- ፖ.ሣ.ቁ 13336
- ፋክስ 251-11-6450879
- ኢ-ሜል eth@mf.iaaf.org
- Website www.eaf.org.et
- ☎ 251-11-6479579

  251-11-6479676

  251-11-6479596

  251-11-6479131

  *<u>ጉርድ ሾላ</u>*
  *<u>አዲስ አበባ</u>*


## <u>ጥቅል ፕሮግራም</u>

- *ታህሳስ 6/2011 ዓ.ም. የቴክኒክ ስብሰባ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ቢሸፍቱ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፤*
- *ታህሳስ 7/2011 ዓ.ም. ውድድሩ የሚካሄድበት ቀን፤*

# 5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር ሕግና ደንብ

## *አንቀጽ አንድ*

## *ዓላማ*

1. ለክልልና ከተማ አስተዳደር ክለብ ተቋማትና የግል ተወዳዳሪ አትሌቶች የውድድር ዕድል ለመፍጠርና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት፤

## *አንቀጽ ሁለት*

## *አጠቃላይ የውድድሩ ደንብ*

1. ይህ ውድድር 5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር ተብሎ ይጠራል፡፡
2. 5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር በበላይነት የሚመራው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ነው፡፡
3. ውድድሩ የሚመራው በIAAF እና በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህግና ደንብ ነው፡፡

## *አንቀጽ ሦስት*

## *የውድድሩ ርቀት፣ ቀን፣ ቦታና ሰዓት*

1. የውድድሩ ርቀት 30 ኪ.ሜ. ነው፡፡
2. ውድድሩ የሚካሄደው ታህሳስ 7/2011 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ ይሆናል፡፡
3. ውድድሩ የሚካሄደው በኦሮሚያ ቢሾፍቱ፣ ሆራና ባቦጋያ ሐይቅ ነው፡፡

## *አንቀጽ አራት*

## *የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር*

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት የመወዳደሪያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፡፡ ቁጥሩ የሚለጠፈው በደረትና በጀርባ ላይ ነው፡፡ ያለመወዳደሪያ ቁጥር መወዳደር አይቻልም፡፡ የመወዳደሪያ ቁጥር በቴክኒካል ስብሰባ ቀን ይሰጣል፡፡

## *አንቀጽ አምስት*

## *አለባበስ*

ማንኛውም አትሌት የክልሉን፣ የከተማ አስተዳደሩን የተቋሙን ወይም የክለቡን መለያ የሆነውን የስፖርት ልብስ መልበስ አለበት፡፡ ማልያ ለብሶ ያልቀረበ ተወዳዳሪ በውድድሩ ላይ መካፈል አይችልም፡፡ ተካፍሎ ቢገኝ የግሉም ሆነ የቡድኑ ውጤት ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## ተሳታፊዎች

ውድድሩ በሁለቱም ፆታ በሴትና በወንድ ተከፍሎ ሁሉም ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦችና የግል አትሌቶች ይሳተፋሉ፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## ምዝገባ

1. እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ቡድን በሁለቱም ፆታ ከ4-12 አትሌቶች ማስመዝገብ ይችላል፡፡
2. የምዝገባ ጊዜ ህዳር 17 እስከ ህዳር 27/2011 ዓ.ም. ድረስ ይሆናል፡፡ ዘግይተው የሚመዘገቡ ክልሎች እና ክለቦች ህዳር 28/2011 ዓ.ም. ብቻ እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) በመክፈል መመዝገብ ይችላሉ፡፡ ከቀነ ገደቡ ውጪ ምዝገባ አይከናወንም፡፡
3. ለውድድሩ ተመዝግበው የሰረዙ /የማይሳተፉ/ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች በቂ ምክንያት ወይም ማብራሪያ ካላቀረቡ በስተቀር ብር 1,000.00 (አንድ ሺ ብር) ይቀጣሉ፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## ክስና ይግባኝ ስለማቅረብ

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ውድድሩ ከመጀመሩ ከ30 ደቂቃ በፊት ነው፡፡
2. የውድድር ውጤቶችን ወይም የውድድር ተግባር ሁኔታን በተመለከተ የክስ ጥያቄ የሚቀርበው ውጤቱ ይፋ በሆነ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
3. ማንኛውም የክስ ጥያቄ መጀመሪያ የሚቀርበው ለውድድሩ ዋና ዳኛ (refree) በቃል በአትሌቱ፣ በአሠልጣኙ ወይም በቡድን መሪው አማካይነት ሊሆን ይችላል፡፡ የውድድሩ ዋና ዳኛው ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ አካል በጽሑፍ ከብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) ጋር ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ዳኛው ውሳኔ በሰጠ በ30 ደቂቃ ውስጥ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. ክሱ በክስ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርቶ ተገቢ ክስ ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ሆኖ ክሱ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ብር ለፌዴሬሽኑ ገቢ ሆኖ ውሳኔው የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## ያልተገባ ፀባይ

ማንኛውም አትሌት፣ አሰልጣኝ፣ የቡድን መሪ፣ ወጌሻ ወይም ሌሎች የቡድን አባላት ውድድሩ በሚከናወንበት ወቅት ያልተገባ ፀባይ ካሣየና ውድድሩን በሚመሩ ዳኞች ወይም የውድድር አዘጋጆች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተዘጋጀው የአሠልጣኞች፣ አትሌቶችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ደንብ አንቀጽ አስር መሠረት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ አስር*

## *የግል/የቡድን ውጤትንና ሽልማትን በተመለከተ*

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ ክልል ፣ ክለብ በአንድ ላይ በመወዳደር በሚያስመዘግቡት ውጤት ወይም ደረጃ መሠረት ውጤታቸው ይመዘገባል፡፡ በቡድን ውጤት አሰጣጥ ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ ቁጥር የገባበት ደረጃ ተደምሮ አነስተኛ ነጥብ ያስመዘገበ ቡድን የውድድሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡ ሁለት ቡድኖች የውጤት ድምራቸው እኩል ከሆነ መጨረሻ ነጥብ ያስመዘገበ ወይም ለአንደኛው የቀረበ አትሌት ቡድን የውድድሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡

**ለምሳሌ**:- ቡድን ሀ. 1ኛ፣ 5ኛ፣ 8ኛና 12ኛ ቢወጡ ድምራቸው 26 ይሆናል፡፡

ቡድን ለ. 2ኛ፣ 3ኛ፣ 6ኛና 10ኛ ቢወጡ ድምራቸው 21 ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት የ“ለ" ቡድን የውድድሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የውጤት ድምራቸው እኩል ቢሆን መጨረሻ ነጥብ ያስመዘገበ (ዘጊው አትሌት) ማለት ለአንደኛው የቀረበ አትሌት ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡

**ለምሳሌ**:- ቡድን ሀ. 1ኛ፣ 5ኛ፣ 8ኛና 9ኛ ቢወጡ ድምራቸው 23 ይሆናል፡፡

ቡድን ለ. 2ኛ፣ 3ኛ፣ 6ኛና 12ኛ ቢወጡ ድምራቸው 23 ይሆናል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ቡድኖች ነጥባቸው እኩል ቢሆን ለአንደኛው የቀረበው የመጨረሻው (ዘጊው አትሌት) 9ኛ የወጣ የ“ሀ" ቡድን ስለሆነ የ“ሀ" ቡድን የውድደሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡

2. ለእያንዳንዱ ቡድን ለውድድር ከተመዘገቡት 12 አትሌቶች በቅድሚያ ውድድሩን ላጠናቀቁ “4" አትሌቶች ብቻ የደረጃ ውጤት ይያዛል፡፡
3. ከ1ኛ እስከ 3ኛ ለሚወጡ ለሁለቱም ፆታዎች
   - የወርቅ
   - የብርና
   - የነሐስ ሜዳሊያ ሽልማት ይሰጣል።
4. በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-10ኛ ለሚወጡ አትሌቶች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
5. ለአሸናፊ ቡድኖች በሁለቱም ፆታ የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፡፡

## *አንቀጽ አስራ አንድ*

## *የተወዳዳሪ ለውጥ*

የተወዳዳሪ ለውጥ የሚደረገው ውድድሩ ከመደረጉ ከአንድ ቀን በፊት እስከ ቀኑ 6፡00 ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የሚጠየቀው ቅያሪ ተቀባይነት የለውም፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሁለት*

## *ዕድሜ*

ማንኛውም የማራቶን ተወዳዳሪ ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያም በላይ መሆን አለበት፡፡ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ተወዳዳሪ በውድድሩ መሳተፍ አይችልም፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሦስት*

## *የአትሌቱ ጤንነት*

በውድድሩ ተካፋይ የሚሆን አትሌት ጤናው የተሟላ መሆን አለበት፤ ጤናው ያልተሟላ አትሌት ተሰልፎ ቢገኝና ጉዳት ቢደርስበት ተጠያቂ የሚሆነው ክልሉ/ከተማ መስተዳድሩ፣ ክለቡ እና አትሌቱ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ አራት*

## *የዶፕንግ ምርመራ*

ከውድድር በፊት እና ከውድድር በኋላ የዶፕንግ ምርመራ ይኖራል ማንኛውም አትሌት ለምርመራ መተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## *አንቀጽ አስራ አምስት*

## *በስም ጥሪና ሽልማት ቦታ በሰዓት መገኘት*

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ45 ደቂቃ በፊት በስም ጥሪ ቦታ በመገኘት ለውድድሩ ዝግጁ መሆኑን ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳወቅ ይኖርበታል፤ በስም ጥሪ ቦታ ተገኝቶ ስሙን ለስም ጠሪ ዳኞች ያላሳወቀ አትሌት በውድድሩ ላይ መካፈል አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡
2. ተሸላሚ አትሌቶች በሽልማት ቦታ ላይ የክልላቸውን፣ የከተማ አስተዳደራቸውንና የክለባቸውና የተቋማቸውን መለያ ለብሰው መቅረብ አለባቸው፡፡
3. የሜዳሊያም ሆነ የገንዘብ ተሸላሚዎች በሽልማት ቦታና ሰዓት ካልተገኙ ሽልማቱ አይሰጣቸውም ፡፡ ነገር ግን ያስመዘገቡት ውጤት ለቡድናቸው ይመዘገባል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ስድስት*

## *የቴክኒክ ስብሰባ*

1. የቴክኒክ ስብሰባ ታህሳስ 06/2011 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ቢሸፍቱ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አዳራሽ ይሆናል፡፡
2. በስብሰባ ላይ የሚገኙት አንድ ቡድን መሪና አንድ አሠልጣኝ ብቻ ይሆናሉ፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሰባት*

## *የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ቡድን ኮታ*

1. የትግራይ ክልል 7 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
2. የአማራ ክልል 7 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
3. የኦሮሚያ ክልል 7 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
4. የደቡብ ክልል 7 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
5. የአዲስ አበባ አስተዳደር 7 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
6. የሐረሪ ክልል 4 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
7. የድሬዳዋ አስተዳደር 4 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤

ክልሎችና ከተማ አስተዳድሮች ከተሰጠው ኮታ ውጪ ተጨማሪ የሰው ኃይል የሚያሳትፉ ከሆነ በራሳቸው ወጪ መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

# 5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ተወዳዳሪ አትሌቶች

## መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር/ክለብ/ተቋም ___________________________

| ተ.ቁ. | ሴቶች | ተ.ቁ. | ወንዶች |
|---|---|---|---|
| | የአትሌቷ ስም | | የአትሌቱ ስም |
| 1. | | 1. | |
| 2. | | 2. | |
| 3. | | 3. | |
| 4. | | 4. | |
| 5. | | 5. | |
| 6. | | 6. | |
| 7. | | 7. | |
| 8. | | 8. | |
| 9. | | 9. | |
| 10. | | 10. | |
| 11. | | 11. | |
| 12. | | 12. | |

**ቅጹን የሞላው**

ስምና ፊርማ ______________

ኃላፊነት _____________

ቀን _______________

# የ5ኛው የ30 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር ኘሮግራም

ቀን፡- 7/04/2011 ዓ.ም.

ቦታ፡- ቢሸፍቱ

| ሰዓት | ክንውን | አፈፃፀም |
|---|---|---|
| 12፡30 | የውድድሩ ስፍራ ለተመልካች ክፍት ይሆናል | በኦሮሚያ ክልል ቢሸፍቱ ከተማ |
| 1፡00 | የሴቶች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 1፡15 | የወንዶች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 1፡30 | የሴቶች/የቬትራን/ ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 1፡50 | የወንዶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| *4፡30* | *የሴቶች የሜዳሊያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል* | *በሽልማት ኮሚቴ* |
| *4፡45* | *የቬትራን የሜዳሊያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል* | *በሽልማት ኮሚቴ* |
| *5፡00* | *የወንዶች የሜዳሊያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል* | *በሽልማት ኮሚቴ* |
| *5፡15* | *የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል* | *በሽልማት ኮሚቴ* |
| *5፡30* | *የውድድሩ ፍፃሜ ይሆናል* | *በሽልማት ኮሚቴ* |

**የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን**